# የማዕድን ሥራ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 273/2013 ዓ.ም

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## የማዕድን ሥራ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

### ዓላማ

የማዕድን ሥራ ፈቃድ የማመልከቻ መመዝገቢያ የክፍያ መጠንን መወሰን በማስፈለጉ፣

በማዕድን ዘርፍ ኢንቨስትመንት ለመሠማራት ለሚፈልግ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ጠያቂ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 እና በማዕድን ደንብ ቁጥር 182/1986 የገንዘብ አቅም ማገስጫ የሚቀርብበትን ሁኔታ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በባለፈቃዶች ሊያዙ የሚችሉ የፈቃድ ክልሎችን ስፋት ጣሪያ ስለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1/1988 ተራ ቁጥር 1 (የከበሩ ማዕድናት ምርመራ ፈቃድ ክልል ስፋት) እና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን የማምረት ፈቃድ ክልል ስፋት ለአንድ ሰው ጣሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

ቀደም ሲል በመንግሥትም ሆነ በግል ኩባንያዎች በተከናወነ የማዕድን ፍለጋ እና/ወይም ምርመራ ሥራ የከበሩ ወይም ብረት ነክ ማዕድናት ምልክት እና ክምችት መኖሩ የተረጋገጠ መረጃ ባላቸው ቦታዎች ላይ የሚቀርብ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ጥያቄ የሚስተናገድበትን አግባብ መወሰን በማስፈለጉ፣

የማዕድን ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ሰው በአብዛኛው ወይም በአናሳ የአክሲዮን ድርሻ በተለያዩ ስሞች አመልክቶ እና ይዞ የሚገኘው የፈቃድ ክልል ስፋት ከተፈቀደው ጣሪያ እንዳያልፍ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የማዕድን ሥራ ፈቃድ የተሰጠባቸውንና ማመልከቻ የቀረበባቸውን ቦታዎች የሚያመለክት ካርታ (License and Application map) በGIS shape file format፣ በPDF file format እና በA4 መጠን ወረቀት በአገልግሎት ክፍያ ለጠያቂዎች መስጠት በማስፈለጉ፣

ማዕድን ሚኒስቴር በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ (2) አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ለማውጣት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ ጠቅላላ
### አንቀጽ 1
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የማዕድን ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ የወጣ የማዕድን ሚኒስቴር የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 273/2013 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2
### ትርጓሜ

በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 2 እና በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1985 አንቀጽ 2 ሥር የተተረጐሙት ቃላት በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡



ስንቅነሽ እጅጉ
ሚኒስትር

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum
ARCHIVES
Ministry of Mines

ከዚህም በተጨማሪ፣

1. "የማዕድን ሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ" ማለት ማንኛውም ሰው የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ሲያቀርብ የሚከፍለው የመመዝገቢያ ክፍያ ነው፡፡

2. "የገንዘብ አቅም" ማለት ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ ሰው ቢያንስ በመጀመሪያው ዓመት ሊያከናውን ላቀደው የሥራ ፕሮግራም ተመጣጣኝ የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡

3. "የማዕድን ክምችት ምልክትና የተረጋገጠ መረጃ ያለው ቦታ" ማለት በመንግሥትም ሆነ በግል ባለፈቃዶች ቀደም ሲል በተከናወነ የማዕድን ምርመራ ሥራ የከበሩ፣ ብረት ነክ ማዕድናትና እንዳስፈላጊነቱ የሌሎችም ማዕድናት ምልክት እና ክምችት መኖሩን የሚያስረዳ የተረጋገጠ የጂኦ-ሳይንስ መረጃ ያለው ቦታ ነው፡፡

4. "አመላካች ካርታ (License and Application map)" ማለት የማዕድን ሥራ ፈቃድ የተሰጠበትን እና ማመልከቻ የቀረበበትን ቦታ የሚያሳይ በShape file format ወይም በPDF file format ወይም በA4 የወረቀት መጠን በባለቀለም ወይም በነጭና ጥቁር ቀለም የተዘጋጀና በመለያ ቁጥር የተመዘገበ ካርታ ነው፡፡

5. "ወቅታዊ የተደረገ ካርታ" ማለት የማዕድን ፈቃድ የተሰጠበትና ማመልከቻ የቀረበበትን የሚያሳይ ካርታ ሲሆን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚመለከተው ክፍል በየ15 ቀን ወቅታዊ የተደረገ መረጃ (የባለፈቃዱ ወይም የአመልካቹ ስም፣ የፈቃድ ቦታውን ቅርጽ ካርታና የማዕድኑን አይነት ብቻ የያዘ መረጃ) የያዘ ማለት ነው፡፡ የካርታው መለያ ቁጥር በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ በሚሰጥር የሚሰጥ ነው፡፡

6. "ደረጃ አንድ የፈቃድ ክልል ስፋት (Category 1)" ማለት የፈቃድ ክልሎችን ጣሪያ ለመወሰን የወጣ የማዕድን ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 1/1988 መሠረት የተከለለ የግሪንስቶን ቤልት አካባቢን የሚያሳይ ቦታ ነው፡፡

7. "ደረጃ ሁለት የፈቃድ ክልል ስፋት (Category 1)" ማለት የፈቃድ ክልሎችን ጣሪያ ለመወሰን የወጣ የማዕድን ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 1/1988 መሠረት የተከለለ ከግሪንስቶን ቤልት ክልል ውጪ ያሉ አካባቢዎችን የሚያሳይ ነው፡፡

8. "የአክሲዮን ድርሻ" ማለት አንድ በሕግ የተቋቋመ ሰው በጋራ ካቋቋሙት የሀብት ባለቤቶች ባለድርሻ ከሆኑ ወገኖች የሃብት ባለቤትነት በነጠላ ዋጋው እኩል ዋጋ ያለው የሃብት መዋጮ ወይም በግዢ የተገኘ የተሳትፎ ድርሻ ነው፡፡

## አንቀጽ 3
## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማዕድን አዋጅና ደንብ መሠረት በማዕድን ዘርፍ የሚሰማሩ አመልካቾችን በተመለከተ ፈቃድ ከማውጣት፣ ከማደስ፣ ከማሻሻልና መብትን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡



ስንቅንሽ እጅጉ
ሚኒስትር

ARCHIVES
Ministry of Mines
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## ክፍል ሁለት
## አንቀጽ 4

## ስለማመልከቻ ምዝገባ ክፍያ፣ የገንዘብ አቅም ማረጋገጫ ማስረጃ ስለማቅረብ እና የፈቃድ ቦታዎች መረጃ ለማግኘት ስለአገልግሎት ክፍያ

### 1. ስለ ማመልከቻ ምዝገባ

1.1. ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው በተዘጋጀው የማመልከቻ ፎርም መሠረት የተሟላ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ሲያቀርብ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 12(1)ሀ መሠረት የማይመለስ የመመዝገቢያ ክፍያ ብር 500.00 (አምስት መቶ) ይከፍላል::

1.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1.1. መሠረት የመመዝገቢያ ክፍያ የፈጸመ አመልካች ማመልከቻው ወዲያውኑ ተመዝግቦ የምዝገባ ቀንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጠዋል::

1.3. ሌሎች በማዕድን አዋጅ እና በማዕድን ደንብ የተደነገጉ ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር የፈቃድ ማመልከቻ ምዝገባ ብቻውን አመልካቹን ፈቃድ ለማግኘት ብቁ አያደርገውም::

### 2. የገንዘብ አቅም ማረጋገጫ ስለማቅረብ

2.1. ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የምርመራ ወይም የማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት በሚያመለክትበት ወቅት በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 11/1 መሠረት የገንዘብ አቅም ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

2.2. ከላይ በተራ ቁጥር 2.1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ያመለከተ ሰው ማመልከቻው ተመዝግቦ የጠየቀው ቦታ በወቅቱ ብቸኛ መብት የሚያሰጥ ፈቃድ ያልተሰጠበት ወይም በቅድሚያ ማመልከቻ ያልቀረበበት መሆኑ እንደተረጋገጠ ለመጀመሪያው ዓመት ያቀደውን የሥራ ፕሮግራም ለማከናወን የተመለከተውን የወጪ መጠን በታወቀ የኢትዮጵያ ባንክ በኢትዮጵያ ብር ገቢ የተደረገ የገንዘብ አቅም የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

### 3. ስለፈቃድ ቦታዎች መረጃ አሰጣጥና የአገልግሎት ክፍያ መጠን ስለመወሰን

3.1. ማንኛውም ሰው የማዕድን ሥራ ፈቃድ የተሰጠበትንና ማመልከቻ የቀረበበትን ቦታ አመላካች የሆኑ እና ወቅታዊ የተደረገ ካርታ (License and Application map) በGIS Shape file format (የባለፈቃዱ ወይም የአመልካቹ ስም፣ የፈቃድ ቦታውን ቅርጽ ካርታና የማዕድኑን አይነት ብቻ የያዘ መረጃ) እንዲሰጠው በሚጠይቅበት ወቅት ከመረጃ ደህንነት አንፃር በዚህ መልክ አገልግሎት ለጊዜው መስጠት አይቻልም::

3.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.1. የተጠቀሰውን አመላካች ካርታ (License and Application map) በA4 የወረቀት መጠን በባለ ቀለም ካርታ ወይም በPDF file



ሲንቅነሽ እጅጉ
ሚኒስትር

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum
ARCHIVES
Ministry of Mines

format እንዲሰጠው በጽሁፍ የሚያመለክት ማንኛውም ሰው እንደ ቅደም ተከተላቸው ብር 100 (አንድ መቶ) ወይም 150.00 (አንድ መቶ ሃምሣ) ወይም በA4 ወረቀት መጠን በነጭና ጥቁር ካርታ እንዲሰጠው በጽሑፍ የሚያመለክት ማንኛውም ሰው ብር 50.00 (ሃምሣ) ሲከፍል በዚህ መመሪያ መሠረት ወቅታዊ የተደረገ የኢትዮጵያ ካርታ አንድ ጊዜ ብቻ ይሰጠዋል።

3.3. ማንኛውም ሰው የተሟላ ማመልከቻ እስካላቀረበ ድረስ በተወሰነ የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት በተከለለ ቦታ ላይ ቀደም ሲል ፈቃድ ያልተሰጠበት ወይም ማመልከቻ ያልቀረበበት ክልል ስለመሆኑ እንዲረጋገጥለት አገልግሎት መጠየቅ አይችልም።

3.4. በዚህ መመሪያ መሠረት ወቅታዊ የተደረገ በA4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጅ ባለ ቀለም አመላካች ካርታ በሥራ ክፍሉ በሚገኝ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ በቁልፍ በሚዘጋ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለተገልጋዮች በሚታይ ሁኔታ በየጊዜው ይለጠፋል።

## ክፍል ሦስት
## አንቀጽ 5

## የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ስለመወሰን

1. የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ስለማሻሻል

1.1. የማዕድን ሥራ ፈቃድ ክልሎችን መጠን ስለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/1988 በተደነገገው መሠረት አንድ ባለፈቃድ ሊይዝ የሚችለው የደረጃ አንድ የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ 2000 ካሬ ኪ.ሜ. በዚህ መመሪያ መሠረት 1500.00 ካሬ ኪ.ሜ. ሆኖ ተሻሽሏል።

1.2. የማዕድን ሥራ ፈቃድ ክልሎችን መጠን ስለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/1988 በተደነገገው መሠረት አንድ ባለፈቃድ ሊይዝ የሚችለው የደረጃ ሁለት የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ 3500 ካሬ ኪ.ሜ. በዚህ መመሪያ መሠረት 2000.00 ካሬ ኪ.ሜ. ሆኖ ተሻሽሏል።

1.3. የማዕድን ሥራ ፈቃድ ክልሎችን መጠን ስለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/1988 በተደነገገው መሠረት አንድ ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ ሊይዝ የሚችለው 5500 ካሬ ኪ.ሜ. አጠቃላይ የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ በዚህ መመሪያ መሠረት 3500.00 ካሬ ኪ.ሜ. ሆኖ ተሻሽሏል።

2. ስለኢንዱስትሪ ማዕድናት ማምረት ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ

የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን የማምረት ፈቃድ ክልል ስፋት በማዕድን ደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀጽ 10/1 እንደተደነገገው ሆኖ ለማንኛውም ዓይነት የኢንዱስትሪ ማዕድን ማምረት ሥራ የሚሰጠው የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከማዕድኑ የክምችት ዕድሜ ወይንም የፈቃድ ዘመኑ ሲያልቅ ከሦስት ጊዜ ሳልበለጠ የሚታደስ የክምችት መጠን የያዘ ክልል ስፋትን ብቻ ይሆናል።

3. በተለያየ የአክሲዮን ስም በአንድ ሰው ሊያዝ ስለሚችል የማዕድን ሥራ ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ



ስንቅነሽ እጅጉ
ሚኒስትር

ARCHIVES
Ministry of Mines
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

አንድ የማዕድን ሥራ ፈቃድ አመልካች ቀደም ሲል ፈቃድ ከተሰጠው ሰው በአብዛኛው ወይም በእናሳ የአክሲዮን ድርሻ ስም በተለያዩ ቦታዎችና ፈቃዶች ስም ድርሻ ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ የሚሰጠው የማዕድን ሥራ ፈቃድ የቦታ ጣሪያ የሚወሰነው የአክሲዮን ድርሻ ካለበት ፈቃድ እና ማመልከቻ ጋር በማገናዘብ የሁሉንም ድምር በማጠቃለል በመመሪያ ከተወሰነው የፈቃድ ክልል ጣሪያ አለማለፉ ሲረጋገጥ ነው።

4. በአንቀጽ 5 ከተጠቀሱት የፈቃድ ክልል ጣሪያ በላይ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ

ከአጭር እና ረጅም ጊዜ አንፃር የሀገሪቱን የማዕድን ኢንቨስትመንት ለመሳብ ወይም የማዕድን ኢንዱስትሪውን ልማት ለማፋጠን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ሲኖረው ይችላል ተብሎ በዓለም የማዕድን ልማት የጎላ ድርሻ ያለውና ተገቢው ማስረጃ የሚቀርብለት አመልካች ወይም ባለፈቃድ ሲኖርና ሲታመንበት በሚኒስቴሩ እየተወሰነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ አምስት ላይ ከተመለከተው የፈቃድ ክልል ጣሪያ በላይ ሊሰጥ ይችላል።

## ክፍል አራት
## አንቀጽ 6

### የተረጋገጠ መረጃ ያላቸውን ቦታዎች ፈቃድ አሰጣጥ ስለመወሰን

1. የተረጋገጠ መረጃና የማዕድን ክምችት ምልክት ያላቸው የከበሩ፣ የብረት ነክ እና እንዳስፈላጊነቱ የሌሎች ማዕድናት ፈቃድ ቦታ ስለመስጠት፣

ቀደም ሲል በመንግሥት ወይም በግል ኩባንያ በተከናወነ የምርመራ ሥራ የተረጋገጠ የከበረ፣ የብረት ነክ እና እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ማዕድናት ዝርዝር ጥናት (Detailed study and known resource) እና ክምችት መረጃ ባላቸው ቦታዎች ላይ የማዕድን ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው በጨረታ ሲሆን አመልካቾች የሚያቀርቧቸው የፕሮጀክት ዶክመንቶች መስሪያ ቤቱ በሚያቋቁመው የገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ በማዕድን ሕጉና ለዚሁ ዓላማ በሚወጣው መስፈርት መሠረት የተሻለ ብቃት ላለው አመልካች ይሆናል።

## አንቀጽ 7
### መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ከጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም.

የማዕድን ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ስንቅነሽ እጅጉ
ሚኒስቴር

ስንቅነሽ እጅጉ
ሚኒስትር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum